የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
አዲስ አበባ/ADDIS ABABA

# ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠ መግለጫ

## አንድ፦ የባንኮች መጠባበቂያና የብሔራዊ ባንክ የማበደሪያ ወለድ ምጣኔን በተመለከተ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ከተሰጡት ተልእኮዎች መካከል የገንዘብ ፖሊሲ በመቅረፅ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረውን የገንዘብ መጠን የዋጋ ንረትን የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ ዋናው ነው። እንደሚታወቀው የዋጋ ንረት የብዙ ምክንያቶች ድምር ውጤት ሲሆን፣ የምርት አቅርቦት እጥረት፣ የሎጀስቲክ አለመሳለጥ፣ የገንዘብና የፊዚካል ፖሊሲ አቋም ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የዋጋ ግሽበትን ለመግታት መንግሥት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ ቢሆንም፣ ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቷል። ይህም ታውቆ አስፈላጊው የፖሊሲ ማሻሻያ መደረግ እንዳለበት በመታመኑ፣ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረውን የገንዘብ ሥርጭት ለመቀነስ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቁጥብ የገንዘብ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ወስኗል።

ስለሆነም፣ እ.ኤ.አ. ከመስከረም 1፣ 2021 ጀምሮ፦

1. ባንኮች ከሚሰበስቡት የተጣራ ቁጠባ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲያስቀምጡ የሚገደዱትን የመጠባበቂያ መጠን ከነበረበት 5 በመቶ ወደ 10 በመቶ ከፍ እንዲል ተወስኗል፤
2. ባንኮች ለአጭር ጊዜ የሚገጥማቸዉን የገንዘብ እጥረት ለመፍታት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚበደሩበት ዓመታዊ ወለድ ምጣኔ ከ13 በመቶ ወደ 16 በመቶ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

ይህ ቁጥብ የገንዘብ ፖሊሲ እርምጃ እየተባባሰ የመጣዉን የዋጋ ንረት ችግር ለመግታት አዎንታዊ ሚና የሚጫወት ሲሆን፣ በአንፃሩ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅእኖ እንደማያስከትል ግንዛቤ ተወስዷል።

## ሁለት፦ የውጪ ምንዛሪ አጠቃቀምን በተመለከተ

የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ከማሳደግ አኳያ በትኩረት መሥራት እንደተጠበቀ ሆኖ የተገኘውን የውጭ ምንዛሬ በአግባቡ መጠቀም ደግሞ ሌላው መሰረታዊ ጉዳይ ነው። በዚሁ መሠረት በባንኮች በኩል በሚገኝ የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀም ላይ ማሻሻያ ተደርጓል።

ይኸውም፦



አድራሻ: ሱዳን ጎዳና: Address: Sudan Street | ፖ.ሣ.ቁ.: P. O. Box: 5550/2048 | ፋክስ: Fax No.: +251-11-551-4588 | ስልክ ቁጥር: Tel. No.: +251-11-551-7430 | Website: www.http://nbe.gov.et SWIFTCODE - NBETETAA